# የዕድሜ አዛውንቱ የፖለቲካ ኩታራ

እንደ እውነቱ ከሆነ የሚከተለውን አስተያየት ለመፃፍ የተነሳሳሁት የፅሁፍ ችሎታ ኖረኝ አይደለም፤ ሆኖም ግን ሰው በሀገሩ ጉዳይ ሀሳቡን ማካፈል ብቁ ለተባሉ ብቻ ይሁን ብየ አላምንም። በተለይ ደግሞ ለነዚህ መብቶች መከበር ሲል የተዋደቀው የዚያ ትውልድ ዓባል በመሆኔ እጅግ የምኮራና ዝምታ ወርቅ ነው በሚለው አባባል የማላምን በመሆኔም ነው ። ስለዚህ የአንድ ሳንቲምም ብትሆን የትኛውንም ክፍል የማትወክል የግል ሃሳቤን ከመሰንዘር መታቀብ አይቻለኝም። መጣጥፌ የግለሰብ አስተያየት ላይ እንጅ ግለሰብ ላይ ያነጣጠረ እንዳልሆነ እንዲታወቅልኝ አሳስባለሁ።

አስተያየቴ እንዳቀርብ ያነሳሳኝ ሰሞኑን ኢሕአፓ ላይ የተከፈተ የአሉባልታ ዘመቻ በመታዘቤ ነው። ፓርቲውን ማጥቃት አሁን የተጀመረ ነው በሚል ወይም ለምን ተከሰተ በሚል ደንቆኝ ሳይሆን፣ የአጥቂዎቹ ስብጥርና የተለያዩ ክፍሎች ስም ያልተሰጠው ግንባር ፈጥረው ስለተነሱበት ነው። በኔ ግምት ይህ መቸም ዝም ብሎ ከገዋ የተፈጠረ ጉዳይ ወይም አጋጣም ነው ብየ አላምንም። ወደ ዋናው ርዕስ ከመግባቴ በፊት ወያኔና ሆዳሞቹ ሰፈር ጫጫታ ሲበዛ የህዝብ ወገንን የሚያደናግጥ ሳይሆን እንዲያውም እሚያበረታታ ሊሆን እንደሚችል ብረዳም፣ በአንፃሩ ደግሞ ምክንያቱ ምን ሊሆኑ ይችላል የሚለውን ማንሳቱ ጉዳት ስለማይኖረው እርግጠኛ ባልሆንም መነሻ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን ጉዳዮች ላንሳና፣

> ኢሕአፓ ጠፍቷል የሚለው የፕሮፖጋንዳ ጦርነት በመክሸፉና እንዲያውም የፖለቲካ ህልውናው አቅም እያገኘ በመምጣቱ፤
>
> የሩቅም ሆነ አገር በቀል ጠላት በኢትዮጵያና ህዝቧ ላይ ከበስተጀርባም ሆነ በገሀድና በረቀቀ ስልት የሚጠነጠነውን ደባ አበክሮ ስለሚያጋልጥ፤
>
> ወያኔ በአገር ውስጥ ኢሕአፓ ዓባላትን እመነጥራለሁ ብሎ ዘመቻ መጀመሩ ህዝብ ዘንድ ባለው ተወዳጅነት የፖለቲካ ህልውናው አቅም ባገኘ ቁጥር አደጋ ነው ብሎ ስለሚያምን
>
> የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሳትላይት ሬዲዮ ስርጭት፣ በአስተማማኝዜና አቅርቦቱና ወደር የለሽ የዜና በትንተናዎቹ፣ በአገር ውስጥ፣በአካባቢ አገሮችና በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ቀዳሚ የዜና ምንጭ መሆኑና አገዛዙ ሊገድበው ቢሞክርም ስርጭቱ ባለመቋረጡ ወደፊት ችግር ያመጣብኛል ከሚል ፍራቻ ሊሆን ይችላል።

ከነዚህ ሁኔታዎች በአንዱም ይሁን በሁሉም ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች በአገዛዙ ውስጥ እየተብላላ የቆየው ድምፅ አልባ ሽኩቻ ጋር ተዳምሮ አሻንጉሊቱን ወያኔ ብቻ ሳይሆን ጌቶቹንም ጭምር እንዳሳሰባቸው አይነተኛ መለያ የሚሆነው ከየስርቻቸው ተጠራርተው ወጥተው በዚያ የፈረደበት ትውልድና ኢሕአፓ ላይ ሰሞኑን ጫጫታውን የተቀላቀሉ አዛውንቶች መታየታቸው ነው። ከነዚህም ውስጥ አስተያየቴ የሚያተኩረው የአንበሳውን ድርሻ የያዙት እድሜ ልካቸውን መሠሪ በሆነ ተመሳሳይ

ተግባር አገሪቱን ያለተከላካይ ለማስቀረት ሲባዝኑ የኖሩት ስመ ጥፉ ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ላይ ነው። ለምን ቢባል፣ በተለያየ ቀለምና ቅርፅ አቀራረብን በመቀያየር ለማህበራዊ ፍትህ የሚታገለው ክፍል ተደማጭነት እንዳይኖረው ከኋላ ሆኖ በተቃዋሚ ሽፋን የሚንቀሳቀሱ አወዛጋቢ ቡድኖችን በመፍጠርና እንዲያም ሲል እንዲጠቁ ማድረግ፣ የአገዛዙ መውደቂያ ሲቃረብም ተቃዋሚ መስለው በመታየት ከደርግም ሆነ ወያኔ ጋር ተለጥፈው የዚያን ትውልድ ታሪክ በማጥቆርም ሆነ ኢህአፓ ላይ ሴራ በመሸረብ የሚታወቁና በየመድረኩ " ዱላ ወይስ መላ" የመሳሰሉትን ትጥቅ አስፈች አሉባልታዎች ሲያሰራጩ የኖሩ ጊዜ የማያስተምራቸው ፍጡር በመሆናቸው ።

በሀገሩ ጉዳይ ብሩህ ተስፋና መልካም ራዕይ ይዞ ለዲሞክራሲያዊ መብት ለታገለው ትውልድ ያላቸውን ጥላቻ ሃይማኖት አርገው እድሜ ልክ ሲገፉ የኖሩ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ትውልድ ጉዳይ አስተሳሰባቸውም መጭውን ትውልድ በክለው ለማለፍ ደፋ ቀና እያሉ ስለሚገኙ ነው። የዚህ ፅሁፍ አላማ እኚህ ሰው ለምን ከዚያ ትውልድም ሆነ ከማንኛውም ክፍል የተለየ የራሳቸው የፖለቲካ ፍልስፍና ኖራቸው፣ ለምንስ የሚለዩበትን አመለካከት ገፉ ከሚል እንዳልሆነ ከወዲሁ ግልፅ እንዲሆን ያስፈልጋል። ጉዳዩ ግን ውድ ህይወቱን ለሀገሩና ወገኑ መብት ሲታገል አሳልፎ የሰጠውን ትውልድ ከእኚህ ሰው በአመለካከት በመለየቱ ብቻ እድሜ ልክ በሃሰት ሲከሱትና ሲያጠቁት በመኖራቸው ነው። ይህ በራሱ አልፎ አልፎ የሚያነሱት የይምሰል ዴሞክራሲ ዲስኩርም ልክ እንደ ሰብአዊ መብት ግንዛቢያቸው ግልብ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ነገራቸው የከፋ ተመፃዳቂ እንደሆኑም ይመሰክራል። ከኢትዮጵያ ህዝብ የትግል አብራክ የተወለደውንና በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ ከማንም አልደራደርም በማለቱ ከመሰል ተምበርካኪ ምሁራን እስከ ጎጠኞች ቢዘምቱበትም ወይ ፍንክች ብሎ መራራውን ትግል የቀጠለው ኢሕአፓ ላይ ተራ አሉባልታን የማናፈስ ስራቸውን አሁንም ቀጥለዋል። የጊዜ ብዛትም የህወሀቱ የቀድሞ ከፍተኛ አመራር የገብሩ አስራትን ግማሽ እንኳ አላስተማራቸውም። እንዲያውም በተቃራኒው ለሀገርና ለወገን ውድ ህይወቱን የከፈለ ወጣት ትውልድ ላይ ይኸው ዛሬም በ11ኛው ሰዓታቸው መቃብሩ ላይ ቆመው የሚሳለቁ የእድሜ አዛውንት የፖለቲካ ኩታራ እንደሆኑ ቀርተዋል።

እኚህ ሰውና መሰሎቻቸው ግራው ትውልድ ይህን አመጣብን ያን አመጣብን በማለት ከነሬጋንና ታቸር በላይ ለካፒታሊስቱ ዘብ የቆሙ የሚመስላቸው ተንበርካኪ ምሁራን ያ ትውልድ አለመመቸቱ እሰየው የሚያሰኝ እንጅ ፊፅሞ የሚከፋ አይደለም። ሃያላን በቀደዱለት ጎዳና ባለመነዳቱ ለሀገርና ለወገን ውድ ህይወቱን የገበረውን ትውልድ ታሪክ በማምታታት ለወታደራዊ አገዛዝ የሃሰት ምስክር ሆነው የቆሙና ያላንዳች የህሊና መሰቅጠጥ እነ መላኩ፣ እርገጤና አሊ ሙሳን የመሳሰሉትን አረመኔዎች ያሰለፈውን ፋሽስታዊ አገዛዝ (ደርግ) "ኢሕአፓ ተንኩሳው ነው" ነው የሚሉት ክፍሎች ህሊናቸውን ገና ከጥዋቱ ሸጠው አገራቸውን እንደ ፍልፈል ከውስጥ ሲሰረስሩ የኖሩ መሆናቸውን እንደማናውቅ ሁሉ፣ ዘመኑ የተገላቢጦሽ ሆነና፣ ዛሬ አይናቸውን በጨው አጥበው ማን ባንዳ ማንስ አርበኛ እንደነበር ምስክር ወረቀት ሰጪ ሆነዋል። ታሪክ ይቅር የማይላቸው ግለሰብ ራሳቸውን ታሪክ ሰሪ አድርገዋል። የተከበረችውን አገር ላዋረዱ ማህበራዊ መሃንዲሶች እነማን እንደከሸፉ ሊያስተማሩ ድረፍረቱን ያገኙበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ሀገራችን ከገጠሟት አሳዛኝ ክስተቶች ውስጥ የሌባ አይነ ደረቆች ሰው የፈራውን እውነት ተናጋሪ ነን ብለው አደባባይ የወጡበት ይኸው ጊዜ ነው።

አሁን በአሜሪካ ከተሞች በመዘዋዎር በኢሕአፓ ላይ እያሰራጩ እንዳሉት አሉባልታ፣ ከአስር ዓመታት በፊት አጋጣሚ ሆኖ በተካፈልኩበት አንድ ስብሰባ ላይ በለመዱት ኢፍትሃዊ አንደበታቸው "የ 15 ዓመት ልጆችን እየላኩ የመንግስት ባለሞያዎችን መግደል (ደም ማፍሰስ) ነው ሌላ ምን ተደርጎ ነው" በማለት ኢሕአፓን ለመወንጀል ከርዕስ ውጪ ሲቀበጣጥሩ፣ ፍርዳቸው ያሳዘነው ከመካከል አንዱ አዳማጭ የሚከተለውን መጠየቁ ትዝ ይለኛል " የእርስዎን አመጣጥ ተከትየ አንድ ጥያቄ እንድጠይቅዎት ይፍቀዱልኝ : ፐ/ር መስፍን የ 15 ቱ ዓመት ወጣት እንዳሉት ገና ልጅ ነው ምናልባትም የሚያረገውን ባለማዎቅ ይሆናል እንበልና፣ እያወገዙ ያሉት የ15ቱን ወጣት ድርጊት ሲሆን፣ የ 40 ዓመቱ የደርግ ባለሟል የ 15 ዓመት ወጣቶችን ስለመግደሉ ግን ወንጀል አይደለም እያሉን ነው ማለት ነው? ወይስ ወጣቱን መግደል ወንጀል አይሆንም የሚል ፍርድ እየሰጡ ነው?" ተብለው ሲጠየቁ፣ በጠያቂው አካል ላይ ጉዳት ከማድረስ በመለስ ከተራ ስድብ በማይተናነስ ትዕቢት አዘል ዘለፋን እንደ መልስ መስጠታቸውን አስታውሳለሁ። በመሆኑም ፍትህ የሚባለው ፅንሰ ሃሳብ ሲያልፍ ያልነካቸውና ህሊና የሚባለውን ነገር ያልፈጠረላቸው ግለሰብ ናቸው። የሰው ልጅ ውርደትና መከራን አሜን ብሎ በመቀበል ተረግጦ እንዲገዛ የሚፈልጉ፤ በአንድ በኩል ከኔ በላይ ምሁር ለአሳር የሚሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጓንታቸውን አውልቀው ለፋሺቶች ጠበቃ የሚቆሙ በአንድ ራስ ሁለት ምላስም ናቸው።

ሀገራችን የነበረችበትን የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ በቅንነት ተገንዝበው ገንቢ የሆነ ትችት የሚያቀርቡ ምሁራን በቀላሉ ሊያዩት የሚችሉት የመጀመሪያ ጉዳይ ቢኖር፣ ያ ትውልድ ትግል የጀመረው ምንም አይነት የፖለቲካ ልዩነት በማይስተናገድበት፣ ዜጎች ፍፁምና "ስዩመ እግዚያብሄር" ለሆኑት ንጉሥ ፀጥ ለጥ ብለው መገዛት አለያም እጣቸው ስቅላት ወይም ግዞት በሆነበት፣ የዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ ተመክሮም ሆነ የቅራኔ አያያዝ ስልት ገና ዳዴ እንኳ ባላለበት ፣ ሀገራቸው ከኋላ ቀርነት የምትወጣበትንና ዜጎቿም የወደፊት እጣዋ ባለቤት የሚሆኑበት ዴሞክራሲያዊ አገር እንድትሆን ብሩህ ተስፋ ይዞ የተነሳ ትውልድ መሆኑነወ ይረዳሉ። ነገር ግን ገና ከመነሳቱ የሻጠሩና ወደፊት ሲባሉ ዘለው ባለፈው ላይ መንጠላጠልን ከሚያዘወትሩ ጨለምተኞች ውስጥ ያኔም እንዲሁ ነበሩ። ሁሌም አሁን ካለውና እኒህ ሰው ከተመቻቹበት አብዛኛው ህዝብ ሰጭ ጥቂቶች ደግሞ ወሳጅ የሆኑበት ኢኮኖሚያዊ-ማህበራዊ ግንኙነት መለወጥ አለበት ብለው በተነሱ አገር ወዳዶች ላይ ጥላቻና ጨለምተኛ አስተሳሰባቸውን እንደ ታላቅ ራዕይ ሲገፉ የኖሩ ሲሆኑ፣ በአስተሳሰብ ከሚለዩ ዜጎች ጋር ቡጢ ለመግጠም የሚገለገሉና በእድሜ አዛውንት ይሁኑ እንጅ በፖለቲካ ባህሪያቸው ገና በኩታራነት የቀሩ ግለሰብ ናቸው ። አይናቸው በቀኝ ፅንፍ ፖለቲካ ታውሮ ማየት ተሳናቸው እንጅ የዚያ ትውልድ ትግል የወለደው ኢሕአፓ በረዥም ዓመታት ትግል የተመከሮ አንጋፋ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ነው። የአላማውም አልፋና ኦሜጋ የሆነው የወገን ነፃነትና የሀገር ሉአላዊነት እንጅ እንደ አሁኖቹ "ስልጡን ፖለቲከኞች" ሊብራል ምንትስየ በማለት የዚህ ወይም የዚያ ባለጊዜ ያሳቀፈውን ርዕዮት ዓለም ተሸክሞ የሚንገታገት ጌኛ አይደለም።

አሕአፓ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት (ኢድሀቅ) አማካኝነት ከነ መኢሶን ፣ ኢዲዩ፣ ከነነሹና አረጋዊ በርሄ ጋር አንገብጋቢ በሆኑ ብሄራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በህብረት በመስራት አርአያ ሆነ

እንጅ እንደ ፐ/ር መስፍን በቂም በቀል አልደነደነም። አገሪቱ ባለባት አንገብጋቢ ብሄራዊ ጉዳዮች (በተለይም የሀገር ህልውና አደጋ ላይ በወደቀበት ሁኔታ) የአንድነት ሃይልን በስፋት አሰባስቦ በጋራ መቆሙ ቀደም ሲል ብዙ ካደሙት እና ካቆሰሉትም ጋር ቢሆን የሀገር ህልውና መቅደም እንዳለበት ተንዝቦ ህብረትን በገቢር አሳየ እንጅ እንደ እኒህ አዛውንት የአዞ እንባ እያነባ፣ ግራና ቀኝ የሚል ታፔላ እየለጠፈ ሀገሪቱን የጥላቻና የበቀል ደሴት ሊያደርግ አልሞከረም።

በጊዜው ኢሕአፓ ሶቪየትን ሶሻል ኢምሪያሊስት አገር መሆኗንና፣ ሌሎች በክንፏ የገቡ አብዮታዊ ነን የሚሉ ፓርቲዎችንም እንዲሁ የአንድ አባውራ መሪ የመፍጠርን ሂደት በመውቀስ ኢጋለጠ እንጅ ተለጣፊ አልሆነም፡ ኢሕአፓ ከላይ ያቀረበውን ወቀሳ ከማቅረቡ በፊት የአንድ ሰው አመራርን (ዋና ፀሃፊ/ዋና ሊቀመንበር) ከድርጅቱ አስወግዷል። ይህ እርምጃ ለነብርሃነ መስቀል ማፈንገጥ መነሻ ምክንያት ሆኖ ከባድ ዋጋም ከፍሎበታል።

ኢሕአፓ የራሱን የትግል ተመክሮ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በተጨባጭ መርምሮ የአንድ መሪ ፓርቲ መርሆን አስወግዶ መደብለ ፓርቲን መተከሉ አድርጎ የተቀበለው ከነጎ ርባቾቭ የአቅዋም ለውጥ (ግላስኖስት ፐሬስተሮይካ) በፊት በ1976 ዓ.ም እንደነበር እኒህ ሰውና መሰሎቻቸው ፓርቲውን በጭፍን ለማጥቃት እንዲያመቻቸው ሆን ብለው የሚያስዎግዱት ሃቅ ነው።

ደርግ ግንባር ጥሪ አደረኩ ባለበት ወቅት ኢሕአፓ ጥሪውን አልተቃዎመም። እንዲያውም ጥሪው አዎንታዊ እርምጃ መሆኑን ተቀብሎ ግንባሩ ሁሉንም ተቃዋሚዎች እንዲያካትት ጠየቀ እንጅ (በወቅቱ የወጣውን ዴሞክራሲያ ይመለከቷል)።

ኢሕአፓ ከመፈጠሩ በፊት የብሄር ጥያቄ አንስተው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንደነበሩ ቢታወቅም (1960 ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተመሠረተው ጀብሃንና በዋቆ ቡቱ የተመራውን የሜጫና ቱለማ እንቅስቃሴ ይጠቅሷል) ። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን በሚንሊክ ጊዜ የደነቆረ እንዲሉ፣ ሃሰተኛ ምሁራን (ታዋቂ ፀሀፊዎች በአግባቡ የብዕር ኩሊዎች ይሏቸዋለል) ግማሺ ክ/ዘመን ያልሆነውን የትናንት ታሪክ ከልሰው ያ ትውልድ እና ኢሕአፓ ብሄር ብሄረሰብን አመጡብን የሚሉትን ተራ ቅጥፈት እድሜ ሰጥተው አሁንም የዲስኩራቸው መከፈቻ አድርገውታል ።

በቅርብ ጊዜ ባሳተሙት መፅሀፋቸው "የዘመናዊ መክሸፍ ምንጭ የሆነው አብዛኛው ከ 40 ዓመት እድሜ በላይ ያለውና የተማረ የሚባለው ትውልድ ስለ ንስሃ አያስብም፣ በጥፋቱ ደንድኗል፣ …" ይላሉ (አዳፍኔ፡ ፍርሃትና መክሸፍ ገፅ 135) እኒህ ሰው ንስሃ ግቡ እያሉን ነው፤ ይህን መልዕክት የፃፉት መችም ለቻይናዎች ካልሆነ፣ አንድ ትውልድ በፖለቲካ አመለካከቱ ብቻ እንዳወገዙት የኖሩ ግለሰብ እንዴት "ንስሃ" ስለሚባል ባዕድ ቃል አንስተው ታሪካቸውን ለሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን መንገር ደፈሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገር የቆመበትን ምሰሶ እንደምስጥ እየበሉ እንዳሉት ወያኔዎች፣ እኒህ ሰው ከ40 ዓመት በላይና በታች በሚል ከፋፋይ ዝባዝንኬ፣ ወጣቶች ከታላቆቻቸው ተመክሮን እንዳይማሩ ወዳጅ መስለው መርዘኛ ስብከታቸውን ያለሀፍረት ያሰራጫሉ ። ልክ ፖለቲካውን ለወጣቱ ለቀቅ እያሉ

እንደሚሰብኩት አጠያያቂ ዓለማ ያላቸው ግለሰቦች ማለት ነው። ለነገሩ ሁለቱም ከአንድ ወንዝ የተቀዱ ናቸው።

ጊዚያዊ ነኝ ይል በነበረው ወታደራዊ አስተዳደር የ 60 ዎቹን የንጉሡ አስተዳደር ባለስልጣናት ጉዳይ እንዲከታተል የተቋቋመውን መርማሪ ኮሚሽን በበላይነት የመሩና የወታደራዊው ክፍል አማካሪ እንደነነበሩ እኮ ኢትዮጵያዊያን ያውቃሉ። እንድ በወታደራዊ ፋሺቶች የተመተረ ትውልድ፣ ራሱን ለመከላከል በመሞከሩ ብቻ፣ ለፍትህ ባላቸው እጅግ የተንሸዋረረ እይታ በጠብ አጫሪነት በየመድረኩ ሲከሱትና ሲያጥላሉት ይኖራሉ። ዳሩ ግን ጥላቻን ሃይማኖት ትውልድን ሰይጣን ለማድረግ እድሚያቸውን ሙሉ ሲባዝኑ የኖሩ ደካማ ግለሰብ ጭራሽ ስለ ንስሃ ሊሰብኩ ሲዳዳቸው ከአስመሳይ ጥምጥማቸው በታች ያለ እውነተኛ ማንነታቸውን ማጋለጥ እንጅ አግዚኦ! ከቶ ምኑን አመጣህብን በሚል ሊታለፉ አይገባም። ሟችንም ገዳይንም በአንድ የሞራል ቅንፍ ውስጥ ጨፍልቀው መቀበጣጠር የሚያዘወትሩት ያለፈውን የትግል ታሪክ በማበላሸት የወደፊቱ ትውልድ ላይ ያነጣጠረ ተንኮል በመሆኑ እንደ አጉል ባህሪ ተንቆ የሚተው ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ለወገን ፍትህ ሲል የተዋደቀንና አገር ያደማውን ወንጀለኛ በአንድነት ቀላቅለው (የኢትዮጵያ ወጣቶችም እርስ በርሳቸው ተጫረሱ ኢሕአፓ፣ መኤሶን፣ ህወሀት-ወያኔ፣ ደርግ-ኢሰፓ ወዘተ በአዳፍኔያቸው እንደሚነግሩን) ትውልድን የትግል አርአያ በማሳጣት ተስፋ ቆርጦ ለአረመኔ ገዥዎችና ለሚጋልቧቸው ምሁር ነን ባይ መጋዣዎቻቸው ያለ ተቃውሞ ቀፈታቸውን እየሞሉ የሚኖሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሲሉ ነው። በዚህ አይነቱ አሳፋሪ ዘመቻ እነሆ አንድ ትውልድ የመተሩ ወንጀለኞች የልብ ልብ አግኝተው ወንጀላቸውን ለማስተባበል፣ የፈጁትን ትውልድ ተጠያቂ ሊያደርጉ፣ የደርጉ የቀን ጅቦች በጠራራ ፀሃይ ወጥተው እያሽካኩብን ነው።

በመሆኑም ወያኔ ኢትዮጵያን ከያዘበት ጀምሮ ያለማቋረጥ አሰሳና ግድያ በሚያካሂድበትና በደህንነቱ ውስጥ ልዩ ባጀት መድቦ "ኢሕአፓን ክትትል" በሚል የድርጅቱን ዓባላት ናቸው/ሊሆኑ ይችላሉ ባላቸው ላይ በተገኙበት የሚያጠፋበት ያለምክንያት አይደለም። የትኛው ኢሕአፓ ነው ለይምሰል እንኳን የወያኔ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚያውቀው? የኢሕአፓ አመራሮች እነ ፀጋየ ደብተራው፣ አበራሽ በርታ ወይስ በአንድ ትውልድ ደም የተጨማለቁት እነ ፍቅረ ስላሴ? ትናንት ኢትዮጵያ ያፈራቻቸውን ብርቅየ ልጆቿን የመተሩ ዛሬ ከሰው በላ መንጋጋቸው የተረፉትን ለመጨረስ ከዲያቢሎስ ጋር ተጋብተዋል። በወያኔ ድጎማና በነዚህ ህሊና ቢስ ምሁራን እየታገዙም ወንጀለኛ ታሪካቸውን በአደባባይ ማስጣቱን ተያይዘውታል። በአንድ ትውልድ ደም የተጨማለቁት ፋሺስቶች በወንጀላቸውና ማንነታቸው ሳያፍሩ እንዲያውም ዘግናኝ ታሪካቸውን በፅሁፍ አደባባይ ይዘው መውጣታቸው ያለንበትን አሳዛኝ ታሪካዊ ምፀት ግልፅ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ሁለት ወንጀለኞች (ወያኔና የደርግ ርዝረታገሮች በአንድነት) ለሁለተኛ ጊዜ ኢሕአፓን ለማጥቃት ይኸው ጊዜው የኛ ነው ብለዋል። እጅግ አሳዛኝ የሚያረገው ደግሞ ይህ እየሆነ ያለው ልጆቻቸውን በነዚህ የቀን ጅቦች የተነጠቁ ብዙ እናቶች አሁንም ጥቁር እንደለበሱ ባሉበት አገር ላይ ነው።

እንድ ነገር ግን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፤ ይኸውም ጊዜ ይወስድ ይሆናል እንጅ ዕውነተኛ የፍርድ ቀናቸው ይመጣል። ወላድን ያመከነው ታሪካቸውም እንዳይደገም ሆኖ በሰፊው ይፃፋል። ጊዜ እነ

ፒኖቸን (የችሌው)፣ ኤፍሬን ሪዮስ ሞንት (የጓተሜላዎቹ ጀኔራሎችም)፣ እነ ካርሎስ ኢጁኒዮ ቪደስ ካሳኖቫ (የኤል ሳልቫዶር ጀኔራሎች)፣ ሂሰኒ ሃብሬ (የቻዱ ፒኖቼ የሚል ስም  የተሰጠው) ለፍርድ ቀርበዋል። ለእኒህ አይነቶቹ አረመኔ  ግለሰቦች ቁጥር እንጅ አገር አንድ ተከላካይና አምራች ልጆቿን አይደለም ያጣችው። ለነሀ አይነት ፍጡሮች ተጨራረሱ በማለት ይሳለቃሉ እንጅ ፍትህን ያፈነውን ከተነፈገው ዜጋ (በዳይና ተበዳይ) ለይቶ እንዲያዩ የሚያስችላቸው ህሊና አልፈጠረላቸውም። ይህ ኢሰብአዊ ድርጊታቸው ወጣቱ በመደዳ አሰልፈው ውስኪ እየተራጩ ግንባር ግንባሩን እያሉ ወደ ተቆፈረለት ጉድጓድ ሲወድቅ ይሳሳቁ የነበሩትና መንግስቱ በሚባል ቦዘኔ  የሚታዘዙት ብቻ ሳይሆኑ ይህን ወንጀል የሚያስተባብሉ ተማርን ባይ አረመኔዎችም በሞራል ደረጃ የዕልቂቱ ተባባሪ ናቸው።

በ 1983 ዓ.ም የወያኔን ጦር አጅቦ ወደ አዲስ አበባ የገባው መሠሪ አሜሪካዊ ፖል ሄንዝ፣ ሰኔ ወር 1983 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሠራተኞችንና መምህራንን ልደታ አዳራሽ ሰብሰቦ የሆነ ያልሆነውን ሲቀበጣጥር፣ በስብሰባው ላይ ከነበሩ ምሁራን መካከል እንደ ዶ/ር እሸቱ ጮሌና ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ ያሉት ወያኔን ለዚህ ያደረሰና ለኢትዮጵያ መጥፋት ዋነኛ ተጠያቂ እንደሆነ በመረረ ቋንቋ ገልፀው፣ አማራውን ጠላት በማድረግና ወያኔን በማበረታታት ኢትዮጵያን የማፍረስ እኩይና ከፋፋይ ተግባሩን በመረጃ አስደግፈው በማቅረብ ሲያጨናንቁት በነበረበት በዚሁ ስብሰባ ላይ፣ ፕ/ር መስፍን አንገታቸውን አቀርቅረው ተቀምጠው እንድም ነገር ትንፍሽ ሳይሉ መውጣታቸውን መካድ አይችሉም። ለነገሩ የኒህ ሰው ጥላቻ  ከኢሕአፓም  አልፎ አማራ የሚባል ጎሳ የለም ስለሚሉም አማራውን ያጠቃ ከነበረው ፖል ሄንዝ ጋር ቢዘመዱ ምኑ ይገርማል ። በዚህ ላይ ወትሮም ቢሆን  ከፒስኮሮች ጋር በመወዳጀት እኒህን ሰው የቀደመ ማንም አልነበረም።

ነብሳቸውን ይማርና፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች (ጊዜ የሰጠው ቅል .. እንዲሉ) ኤርትራን በህገ ወጥ መንገድ ሲያስገነጥሉ በታላቅ ድፍረትና ኢትዮጵያዊ ስሜት ጠንካራ ተቃውሞ በማቅረብ ድምፃቸውን ያሰሙ እሳቸው ብቻ ነበሩ። መክሸፋችንን በእብሪት የሚነግሩን "የአዳፍኔው" መርዶ ነጋሪ ታዲያ ያኔ የት ነበሩ ቢባልስ? የምናገኘው መልስ ወይ እነኮህን በለንደኑ ጉባዔ የኢትዮጵያን እድል ሲወስኑ በሲአይኤው ሰራተኛ በአብዱል አባቦራ አስተባባሪነት ለንደን ለንደን ተገኝቶ ኢትዮጵያን ማፈራረስ ወይም ከመለስ ጋር በቴሊቪዥን መስኮት ቀርቦ አምባገኑንና አፍራሹን እያወደሱ አማራ የለም ማለት።

በደርጉ ቀይ ሺብር የወደቀ ወጣትን ሬሳ ተሻግረው ያስተምሩ የነበሩ ምንም አይነት ሰብአዊ ርህራሄ የሚባል ነገር ያልፈጠረላቸው ግለሰብ አሁን "አዳፍኔ፡ ፍርሃትና መክሸፍ" በሚሉት  ህብረተሰብ ላይ የፖለቲካም ሆነ የሞራል ተግሳፅ የማቅረብና እዚህም እዚያም ከሽፈናል ማለቱ  ከተለመደው መመፃደቅ የሚያልፍ አይደለም። ይልቅስ ፍርዱን ወደፊት ለሚፃፈው ትክክለኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በግል የፖለቲካ ስሜት ለማይነዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ተመራማሪ ምሁራን ብንተውላቸው ሳይሻል አይቀርም። በመፅሀፉ ላይ የተሟላ ትችት የማቅረቡንም እንዲሁ።

ወያኔ ኢሕአፓን በማንኛውም መንገድ መጥፋት አለበት ብሎ ከተገንጣይ ቡድኖች እስከ ማህበራዊ ፋሽስቶች አሰልፎ ደፋ ቀና በሚልበት የአሁን ሁኔታ ፣ ከሰሞኑ ፕ/ር መስፍንም መፅሀፋቸውን

ከማስመረቅ ሌላ ተጨማሪ ዓላማ ለማራመድ እቅዳቸው ውስጥ አስገብተው እንደሚዘዋዎሩ ለማወቅ ኢሕአፓ ላይ ሲያሰራጩ በሰነበቱት የሀሰት ፕሮፖጋንዳ መረዳት ይቻላል። በአንፃሩም ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት በተዘዋዋሪ ለወያኔ እገዛ እያደረጉ መሆኑ የሚሳት መስሏቸው ከሆነ እጅግ ተሳስተዋል። ለነገሩ የፖለቲካው እውቀት በሳቸው ተጀምሮ በሳቸው የሚያበቃ ስለሚመስላቸው ይህን ማየት ይሳናቸዋል።

ከአረመኔው ደርግ ዓባላት ውስጥ እንኳ በመጨረሻው ሰዓትም ቢሆን ተገንጣዮችን ለመቋቋም ከነ ኢሕአፓም ጋር ቢሆን ለጊዜው ልንወዳጅ ይገባል ያሉ ወደፊት አገሪቱ ህልውና ላይ የተቃጣው አደጋ ያሳሰባቸው መኮንኖች ነበሩ። በሌላ በኩል ከትልቁ የትምህርት ተቋም ጋር ያረጁት አዛውንት ፕሮፌሰር ግን የሽግግሌ መንግስት የሚል የባዕድ አደናጋሪ መፈክር ሲረጩ ያደረሱትን ጉዳት ማየት አቅቷቸው አሁንም በሕይወት የተረፉ የኢሕአፓ ዓባላት/አመራር መኖራቸው በራሱ እንደ ባለዛር ያስጎራቸዋል።

በአንድ ወቅት በምንም አይነት ከማንነታቸው ጋር በማይጣጣም ሁኔታ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት (ኢሰመጉ) አቋቋቁመው በመሩ ጊዜ፣ በወያኔ እጅ የወደቁ ( በኋላም ፋሽስቱ ወያኔ በጅምላ የረሸናቸው) የእነ ፀጋዬ ደብተራውን፤ ይስሃቅ፤ ስጦታው፤ በለጠና ሌሎቹን  ስማቸውን እንዲያወጡ በተደጋጋግሚ ሲጠየቁ፣ አንዴ ስለነሱ የማውቀው ነገር የለኝም ፣ በሌላ ጊዜ በጦርነት የተማረኩትን አይመለከትም እና ሌላም ሌላም ስንኩል ምክንያት በማቅረብ ኢትዮጵያዊያንን በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ሰብአዊ መብታቸውን የገፈፉና ጥላቻን ቋጥረው የሚኖሩ ደካማ ግለሰብ ናቸው ።  ለዚህም ነው እኒህ ሰው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ የሚባለውን ድርጅት ያቋቋሙት በእርግጥ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ የሚደርስን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማጋለጥ ሳይሆን ሌላ ሃቀኛ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ተቋም እንዳይነሳ ቦታውን ለመያዝ  ነው ይባል የነበረው።

የአዳፍኔው ፕ/ር መስፍን አቀራረብ በተለያየ ጊዜ ከኢሕአፓ ያፈነገጡ አንጃዎችን ያስታውሰናል። ዋናው ምክንያት ሁሉም አንጃዎች የሚጋሩት አንድ ባህሪ በኢሕአፓ ሰማዕት ስም የሚምሉና ስማችው ሲዘከር የአዞ እምባ የሚያነቡላ በመሆናቸው የታወቁ ናቸው።፣ ነገር ግን የሰማዕትን አደራ የበሉ፣ የተሰውለትን ዓላማ የከዱና የኮበለሉ መሆናቸውን ማየት ተስኗቸውም ሳይሆን፣ አደራ ጠብቆ፣ አርማቸውን አንስቶ ትግሉን ያስቀጠለውን ድርጅት ለማጥቃት እንዲያመችና ተቀባይነትም  የሚስያገኙላቸው ስለሚመስላቸው ብቻ ነው። ለዚህም ነው ትግሉን ያስቀጠለውን ፓርቲ ለማጥቃት የመጀመሪያዎቹ ከደርግ የኋለኞቹ ከወያኔ ጋር የተቃቀፉት። እኒህኛውም ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ እንደሚያንገበግባቸውና ሀገራቸውን እጅግ እንደሚወዱ ይሰብኩናል፣ ግን ደግሞ ዋና ጠላት አርገው የሚታገሉት አገር እያፈረሰ ያለውን ሳይሆን የወደቀላትን ትውልድና በስሟ ከማንም ምድራዊ ሃይል ጋር የማይሞዳሞደውን ፓርቲ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ስለ አጉል አገር ወዳድነት ሲነሳ፣ አንድ "የሚያቃጥል ፍቅር" የሚል በሁለት ፍቅረኞች ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ መፅሀፍ በልጅነት እድሜየ ማንበቤ ትዝ አለኝ። ታሪኩ ስለ ሁለት ፍቅረኞች እጅግ አስገራሚ የፍቅር ህይወት ሲሆን፣ በታሪኩ መጨረሻ ላይ አፍቃሪ ጓደኛዋ ዶ/ር እግረ ፀሃይ የምትባል ፍቅረኛውን በቅናት አንቆ ይገድላታል። እናም ፀሃፊው መፅሀፉን የደመደመው "ዶ/ር

አግረፀሃይን አንቆ የገደላት ቢወዳት ነው ቢጠላት?" በሚል ጥያቄ ነበር። እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ፍቅረኛው መሞት ነው። በመሆኑም ወደዳትም ጠላትም ልዩነት አያመጣም። በተመሳሳይ ሁኔታ እነ ፐ/ር መስፍንንን መሰል ሁሉን አውቃዎችም ይህን የምንለው/የምናደርገው አገራችንን ስለምንወድ ነው እያሉን፣ ግን ጠንክረው ሲታገሉ የኖሩት የሞቱላትን በማጥላላለትና የቆሙላትን ለማጥፋት ሲባዝኑ ነው። አገራችን እነ መንግስቱ ሀይለማሪያምን በመሰሉ አፍቃሪዎች እኮ ደምታለች። የእኒህን ሰው አይነት ፍቅር ይብቃት። የቁርጥ ቀን ልጆቿን በነዚህ አይነት የውስጥ አርበኞች ተነጥቃ በጉማሬዎች መዳፍ ገብታለች። ስለዚህ ከእንግዲህ በቃችሁ ሊባሉ ይገባል።

ፐ/ር መስፍን ከደርግና ወያኔ ፍጅት የተረፉ የኢሕአፓ ዓባላት በህይወት መኖራቸው እጅግ የሚያንገበግባቸው በተፈጥሯቸው ልበ ድፍን ሰው ናቸው ማለት ይቻላል። አሁንም ቢሆን ወያኔ እጅግ የሚጠላውና በማንኛውም መንገድ መጥፋት አለበት ብሎ ከተገንጣይ ቡድኖች እስከ ማህበራዊ ፋሽስቶች አሰልፎ ለማጥፋት ደፋ ቀና በሚልበት በአሁኑ ጊዜ፣ መፅሀፍ በማስመረቅ ሽፋን ሌላ ዓላማ ይዘው እንደሚዘዋዎሩ ለማወቅ ኢሕአፓ ላይ ሲያሰራጩ የሰነበቱት የሀሰት ፕሮፖጋንዳ አንዱ ሲሆን፣ በ1983 የለንደን ላይ እንዳደረጉት ዳግም ከነ ኸርማን ኮኸን ጋር ተሰብስበው ኢትዮጵያን አጣጥለው የኢሳይያሷን ኤርትራ ሲያወድሱ መደመጣቸው ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው። በዋሽንግተኑ ስብሰባ ላይ አሜሪካና እንግሊዝ ተጫኑን የሚለው አቤቱታ ይልቅ እጅግ የተዋጣለት ድራማ ነበር። ይህችን መሰሏ ቀልድ ከአፍሪካ መሪዎች ሁሉ ትልቁ ደንበኛቸው እሱ ራሱ መሆኑን አለም የማያውቅ መስሎት የዓለም ገንዘብ አበዳሪ ተቋማትን በየመድረኩ የሚከሰው ሙሲቬኒ ጋር ታመሳሰላለች።

እውነት የሚጀመረው አንድን ነገር በትክክለኛ ስሙ በመጥራት ነው እንዲሉ፣ ፐ/ር መስፍን እድሜ ልካቸውን የትምህርት ተቋምን ተገን አድርገው ሊታገሉ የተነሱ ዜጎችን ጠልፎ በመጣል ሲያሴሩ የኖሩ ደካማና ፈሪም ጭምር ናቸው። እውነትን በጣም ነው የሚፈሩት። ለዚህም ነው የፖለቲካ ሚናቸውን ሲጠየቁ፣ የጠያቂዎችን አፍ ለመዝጋት ቶሎ ብለው ወደ ተራ ዘለፋ የሚገቡት። በፖለቲካ አመለካከታቸው ከእሳቸው የሚለዩ ሲያጋጥሟቸው ምክንያታዊ መከራከሪያ የሚባል ነገር የማያውቁ፣ በጣም ወርደው ግለሰብን በማጥላላት ማን ነሺና/ነህና በሚል ማንጓጠጥና በማግለል የሚያምኑ ሰው ናቸው። ስለ ንስሃ መግባት ሲሰብኩ መስማት ደግሞ፣ በቀልድ የሚተዳደሩትን ሞያተኞች ገበያ ያላግባብ እንደመሻማት ይቆጠራል። እንኳን ከዚያ ትውልድ ከራሳቸውም ጋር ሳይታረቁ ይኸው የመጨረሻው ኬላ ላይ ደርሰዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከነማክካርቲ በላይ ፀረ-ኮሚኒስት ለመሆን የሚዳዳቸው አዛውንት አዳፍኔ በሚሉት "ከሽፈናል" የጨለምተኛ ጉዟቸውን በዓለም ታዋቂ ከሆነው ግራ ዘመም አሜሪካዊ ምሁር ኖም ቾምስኪ እይታ ጋር ለማዛመድ ያደረጉት ሙከራ ከንቱ አቅጣጫ የማሳት ሙከራ ነው። ታሪካቸውን ጠንቅቆ የሚያውቀው ትውልድ ባለበት ዓለም - ቢሆንም እንኳን በነበርዠንስኪ እንጅ ይህ ከቶ የሚያስኬድዎት መንገድ አይሆንም። ሲቀዘቅዝ በጅ ሲሞቅ በማንኪያ ሊሆንም አይችልም። ትውልድ ይዞ የተነሳቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎች ወደ ጎን ትተው፤ በዋሽንግተን ደንብ ኮሚኒሶት ምንትስየ እየሰነቀሩ ሲሳለቁበት እንዳልኖሩ ዛሬ ቀለም ቀይረው የኤም አይቲውን ስመ ጥሩ ምሁር ዋቢ ሊያደርጉ መከጀል ያልወለደኩት ልጅ አባየ ቢለኝ - እንደሚሉት ይሆናል።

ያዚያን ትውልድ ትግል የመሩ ብርቅየ ኢትዮጵአዊያን ልክ እንዳለፉት አርበኞች አባቶቻቸው መስዋዕት መቀበልን በመስዋዕትነት ያስተማሩ ጀግኖች እንጅ ቀለማቸውን እየቀያየሩ ለመጣው አጋዛዝ እያጎነበሱ በመኖር የሚያምኑ ከንቱዎች አልነበሩም ፣ ማንበብና መመራመርን ቀዳሚና ዋና የትግል አካል አድርገው የተዘጋጁ፣ ንቁና የማለዳ ኮከብ ምሁራን ነበሩ እንጅ እርስዎ ዛሬ ምስክሩ ሁሉ አልቋል ብለው በትዕቢት "የለብለብ" እውቀት ተይዞ በሚል የሚሳለቁበትት ትውልድ እንዳልሆነ እንኳን ኢትዮጵያዊያን ባዕዳንም ያልካዱት ሃቅ ነው ። እንደ እውነቱ ከሆነ በፖለቲካው ዓለም ገብተው እንኳን የ 14 ቱን ክ/ሀገር ህዝብ ከዳር እስከ ዳር ያነቃነቀውን የዚያን ትውልድ ብቃት መጠየቅ ይቅርና ጠፍጥፈው የሰሩትን ቀስተ ደመናን እነኳን በተጨባጭ የመገምገም ትዕግስትና ሃላፊነት ይሰማዎታል ማለት አይቻልም።

እኒህን መሰል ሃሰተኛ አገር ወዳድ ነን ባዮች አብዛኛውን ጊዜ እነሱ ከሚያቁት ውጭ የሆነ አዲስ ራዕይ ወይም የአስተሳሰብ ለውጥን ይፈራሉ። ስለሆነም ምን ይዘውብን መጡ በሚል ማግለልን ይመርጣሉ። በዚህም ምክንያት ለሰው ልጅ ዓመለካከትና አውቀት ክልል ማበጀት ይቀናቸዋል። አፍሪካን ማዕከል ያደረገ እሳቤ ከሚያራምዱ መካከልም አንዳንዶች ልክ እንደርስዎ (ፓን አፍሪካኒስት ነን ከሚሉ ) እንዲሁ ሁሉንም ነገር የፈጠርን አፍሪካዊያን ነበርን ሊሉ ይቃጣቸዋል። በመሆኑም ከዚህ አስተሳሰባቸው አድማስ ሰፋ አድርገው የሚመለከቱና የሰው ልጅ እውቀት በቀለምና በጅግራፊ አይከለልም የሚሉትን በጥርጣሬ ይመለከታሉ። በዚች ምድር ላይ ማንም ክፍል ለሁሉም ስልጣኔ ብቸኛ ባለቤትነት ሊኖረው የሚችል የለም። ዛሬ የሰው ልጅ ለደረሰበት "የስልጣኔ" በአራቱም ማዕዘን እሚገኙ ሕዝቦች አሻራ አለበት። ሀይማኖት ከአድማስ አድማስ እንደሚዛመተው ሁሉ፣ ሳይንስና ፍልስፍናም ተወራራሽ ሀብቶች እንጅ የምዕራባዊያን ወይም የምስራቃዊያን ሆነው እንዲገደቡና ክልል ሊበጅላቸው አይገባም፡፡ የፕሮፌሰሩ አይነት ደካማ ምሁራን የነጭ ምንትስየ ቅብጥርስየ ሲሉ ይደመጣሉ። ሀቁ ግን ይህን ከሚሉት አንዳንዶቹ እንዲያውም የነጮቹን ቆሻሻ ስራ የሚሰሩና የይምስል ስልጣን እየወሰዱም ለጥቁር ህዝብ ምፀት ሽፋን የሆኑ ብዙ እንዳሉ መገንዘብ አይከብድም። መልኩን ይቀይር እንጅ ወደ እኛው አገርም ስንምጣም አማራ የለም የሚሉ ባንድ በኩል፣ ከአማራው በላይ አማራ ነን የሚሉ በሌላ በኩል ቆመው የሚከፋፍሉ ካድሬዎቹን ወያኔ በተቃዋሚው ጎራ አሰማርቶ አክራሪ የሚላቸውን ድርጅቶችና ግለሰቦች እንደሚያስጠቃ ይታወቃል። ይህን ተንኮላቸውን ከ 25 የክህደት ዘመን በኋላ የማናስተውል ከሆነ ወያኔ ይግዛችሁ ተብለን ተረግመናል አለዚያም ተመክሮ እኛ ላይ ሲደርስ ትርጉሙን ቀየሯል ማለት ነው።

አንድ ትውልድ አገሩን ለመታደግ ከሌሎች አገሮች ተመክሮ በመማር ለትግሉ ይበጃል ባለው መርሆ ለሀገሩ የመታገል ታሪካዊ ሙብቱም ሆነ ግዴታው መሆኑን ቅንነት ቢኖራቸው በተረዱት ነበር። ፍፁም ነው የምንለው የስርዓት አይነት ባይኖርም ዘመናዊ ባሪያ ንግድን በሌላ ስም የሚያስኬደውን ካልመረጣችሁ ልንባል አይገባም። ለምሳሌ ደቡብ ሱዳን ከሰሜናዊው ክፍል መገንጠል ዘላቂ ግጭት እንጅ ለዜጎች ነፃነትን እንደማያመጣ ከኤርትራ ውድቀት ቢማሩ ኖሮ ባልደገሙት ነበር። ቢያፍራዎችም እንዲሁ ከሁለቱም ቢማሩ የቆየ መንገዳቸውን በቀየሩ ነበር። ነፃነትን በጎሳና በጅኦግራፊ ክልል ዙሪያ አጥብበው የሚመለከቱ ሁሉ የጉዟቸው መጨረሻ የማያምረውም በዚህ ምክንያት ነው። በተለይም አብዛኛውን ጊዜ ወንድማማች/እትማማች ህዝቦች እንደ ጠላት እንዲተያዩ ከዜጎች ውስጥ መንፈስ

ደካማውን በመጠቀም የሚያመቻቹትም ከፋፍሎ መግዛትን የለመዱ ባዕዳን እንጅ የሀገሬው ተወላጅ እንዳልሆነ ታሪክ ደጋግሞ የሚመሰክረው ሃቅ ነው። ስለዚህ ከሌሎች አገሮች አዎንታዊና አሉታዊ ተመክሮ መማር ብልህነት እንጅ ተቀጥላ መሆን አይደለም። በአሜሪካ ፖለቲካና ኢኮኖሚ የተመራው ፒኖቸም ሆነ ወያኔ ወይም ደግሞ የሶቪየቱ መጋዣ መንግስቱ ሀይለማሪያም ለህዝባቸው ምፅትን እንጅ ደግ ነገር አላመጡም። ስለዚህ ሶስቱም አሻንጉሊት አገዛዞች ከየትኛውም ሃያል ጋር ቢለጠፉ የአፈና ስልታቸው መልኩን ከመቀየር ሌላ ልዩነት ሊኖራቸው አይችልም። ስለዚህ ልዩነቱ ህዝብ ሙሉ ነፃነቱ ተከብሮለት በሚመርጠው ዴሞክራሲያዊ እስተዳደርና ስልጣኑን በነፍጥ ነጥቆ ህዝብን በማሸበር የሚገዛ የአንድ ፓርቲ/ቡድን ህገወጥ አገዛዝ መካከል ነው።

የትኛውም ትውልድ ቢሆን ፕሮፌሰር መስፍን የወረሱትን የፖለቲካ ባህል ወርሶ ለመጣው ገዥ ሁሉ እያጎነበሰ እንዲኖር አይገደድም። የወደፊት የሀገሩን እጣ ወሳኝ በሚሆን ጉዳይ ድምፁን ለማሰማትም እንዲሁ የማንንም ፈቃድ መጠየቅ የለበትም። እያንዳንዱ ትውልድ በጊዜው ለሚገጥሙት ማህበራዊ ችግሮች ምላሽ መስጠትና የራሱን ታሪክ ይሰራ ዘንድ ይጠበቅበታል። እውነቱን እንናገር ከተባለ ለማህበራዊ ፍትህ በሚታገሉ ላይ አቃቂር ከማውጣት ባለፈ ፕሮፎሰር መስፍን ለወደፊት ሀገራቸው ሲሉ (ደካማ የፖለቲካ ስሜታቸውን እንደ ታላቅ ግኝት ከማባዛት ወጥተው) መጭው ትውልድ የሀገሩና የነፃነቱ ባለቤት ይሆን ዘንድ አቅጣጫ ለማስያዝ መልካም አርአያ የሆኑበት አጋጣሚ ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም።

"አዳፍኔ" ግልፅ ያደረገው ነገር ቢኖር እብሪትን እንደ ብስለት ፤ ያልተረዱትን በማጥላላት የእስካሁኑ ጉዞ አልበቃቸው ብሎ ያንኑ ያረጀና እጅ እጅ ያለ ትውልድ ላይ ጥላቻ አሻራቸውን ትተው ለመሄድ ከጊዜ ጋር ግብግብ መግጠማቸውን እንጅ ከታሪክ ተምሮ ማስተርን አያሳይም። በዚሁ መፅሀፍ አንድ በሳቸው የጥላቻ መርዝ የተከተበ ነፈዝ፣ "ፅሁፉን ከተቹት ውስጥ" በሚል ካቀረቧቸው አንዱ፣ (የተለመደ ኢሕአፓ ላይ ተራ ዘለፋና ውሸት ለማሰራጨት እንዲያመቻቸው ብለው ባቀረቡት ግለሰብ በኩል የሚነግሩን ማለት ነው) ፕሮፌሰሩን ጣፆት አድርጎ ከሰገደ በኋላ እንዲህ ብሏል "በደርግ ዘመን ኢሕአፓ የሚባለው ቡድን የእሱን ዓላማ የሚጠይቁትንና የሚቃወሙትን በተለይም መኢሶን የተባለውን የባላንጣውን ቡድን ቀኝ መንገደኛ እያለ ስም በማጥፋት ብቻ ሳይመለስ በጥይትም እንካ ይቀመስላችሁ ይል እንደነበር አስታውሳለሁ" (አዳፍኔ፡ ፍርሃትና መከሸፍ ገፅ 204) ይላል።

መኢሶኖች ገና ወደ አገር ሳይገቡ የሚያቋቸውን የኢህአፓ ዓባላት ስም ዝርዝር ለደርግ ልከው ለወረታቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ አይሮፕላን በረራ ቲኬት ልኮላቸው፣ "ለደርግ ሂሳዊ ድጋፍ እንስጠው" በሚሉት ወራዳ ሰበብ ደርግን ተጠግተው የወታደሩን ከንፍ በሚያስንቅ አረመኔነት ወጣቱን በጅምላ ጭዳ አደረጉ፣ ውስኪ እየተራጩ በዚህ ፅሁፍ ልናነሳቸው የሚዘገንኑ ሰቆቃዎችን በአንድ ትውልድ ላይ ፈፅመዋል። በያዟቸው የኢሕአፓ ዓባላት ላይም ከዚህ መለስ የማይባል ስየል ሲያደርሱ የነበሩ፣ ስንቶቹን እናቶች የወላድ መካን ያደረጉትን የእነ ሰናይ ልኬና ዳንኤልን ቡድን እኮ ነው አዛውንቱ ፕሮፌሰር በሃሳብ ስለተለዩ ኢሕአፓ ገደላቸው ብለው በሁለተኛ ሰው በኩል የሚነግሩን። ለነገሩ መኢሶኖች በደርግ ላይ ያቀረቡት ሂስ ነበረ ከተባለ እንኳን " እኛ እናስራለን እናንተ ትፈታላችሁ" (ሰፊው ህዝብ ድምፅን ይጠቅሷል) ከማለታቸውና ሌላ ቀይ ሽብርን ያረቀቁና የመሩ ከመሆናቸው

በስተቀር ያቀረቡት ይህ ነው ተብሎ የሚጠቀስ ሂስ አልነበረም። በሌላ አነጋገር ደርግ ያሰርናቸውን በመፍታት መለሳለሱን ያቁም በሁሉም ላይ "አብዮታዊ እርምጃ ይወሰድ" በሚል ቅሬታ ማሰማታቸውን የራሳቸው ልሳን የነበረው ጋዜጣ ይመሰክራል።

ይህችን አስተያየቴን በማጠቃለል፡ በኔ አምነት፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውለበለበ ሁሉ ደፍሮ ይቆምለታል ማለት አይደለም፤ ፀረ-ወያኔ ነኝ ያለው ሁሉ ፀረ ወያኔ አይደለም፤ ህብርት ህብረት የሚለው ሁሉ ህብረት ፈላጊ አይደለም፤ ብረት አነሳን ያለው ሁሉ ሊዋጋ ነው ማለት አይደለም፤ የጠመጠመው ሁሉ ቄስ እንደማይሆን፣ ዶ/ር/ፕሮፌሰር ነኝ ያለው ሁሉ የፖለቲካም ሆነ የሞራል ብቃት አለው ማለት አይደለም፣ የኢትዮጵያን ታሪክ/ገድል ያነበነበው ሁሉ ለኢትዮጵያ መልካም ራዕይ አለው ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ከውጊያው ይልቅ ጠላትን መለየቱ ይከብዳል እንደሚሉት፣ ምናልባት እነዚህና እነዚህን መሰል ሁኔታወችን በግምት ውስጥ ካስገባን አስመሳዮችን ከሀቀኛ የሀገሪቱ ወገኖች የመለየቱን ተግባር ሊያቀለው ይችላል ።

እንዲሁም ደግሞ ሳናውቅ በቅንነት በተለያየ ቀለምና ቅርፅ ተነስተው በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ስም የሚምሉ ሃሳዊ መሲሃን እንደበፊቱ የህዝብን ድል ደግመው እንዳያስነጥቁ የቅርብ ጊዜ ተመክሮዎች በሞቅ ሞቅ ሰልፈኞች ሳይድበሰበሱ ለማህበራዊ ፍትህና የሀገር ሉአላዊነት በሚደረገው እንቅስቃሴ ትምህርት ቢወሰድባቸው ከበፊቱ የተለየ ውጤት ማምጣት ይቻላል። የሀገርን ሉአላዊነትና የወገን ክብር በሚነካ ጉዳይ ከማንም ጋር አንደራደርም በማለታቸው ከተገንጣይ ሃይሎች እስከ ቅጥረኛ ምሁራን የሚረባረቡባቸውን የሀገሪቱ የቁርጥ ቀን ልጆችንም ወገን ከጎናቸው ሊቆምላቸው ይገባል።

ዝምታ ለበግም አልበጀ እንዲሉ፣ *አርበኞች ልጆቿ* ጠላትን በተዋጉበት አደባባይ ሲሰቀሉ - ዝም፤ ታጋይ ልጆቿ በጠራራ ፀሃይ ግንባር ግንባራቸውን እየተባሉ ሬሳቸው በየመንገዱ ሲጣል- ዝም፤ እበላ ባይ ምሁራን ፀንተው የቆሙላት ልጆቿን በስደት አምባቸው ሳይቀር መተው ሲሳለቁባቸውም -ዝምታ ከሆነ፣ ባርነትንና ተንበርካኪነትን እንደ መልካም ቅርስ እስከ ወዲያኛው ትውልድም የምናወርስ ህሊና ቢሶች እንዳንሆን ያሰጋናል። ስለሆነም የተገፈፍነውን ብሄራዊ ክብር ለማስመለስ የመጀመሪያውን እርምጃ ዛሬውኑ ወገን ለይተን እንቁም በሚል ወገናዊ ማስታወሻ ልሰናበት።

ከበዛብህ ደበላ